# የ 4 ኛው ዮሃንስ፣የራስ አርአያና የራስ አሉላ ጥላቻን በፍቅር የማሸነፍ የፖለቲካ ዶክትሪን....



ብርሓኑ በረሐ

ራስ አሉላ አባ ነጋ የኤርትራ አስተዳዳሪ በነበሩበት ጊዜ “ፍትሕ እንደ አሉላ” ተብሎላቸው ነበር፡፡እውቁ ጄኔራል አሉላ በቀይ ባሕር በኩል በመሽሎክ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለመናድ የሚመጡ ጠላቶች በማንበርከክ የታወቁትን ያህል የእንደ ግብፅ ያሉ የውጭ ጠላት ተላላኪዎችም በማንበርከክ የተዋጣላቸው ነበሩ ራስ አሉላ፡፡በምድረ ሀማሴን የግብፅ ተላላኪ በመሆን ይሰሩ የነበሩ ደጃት ወልደ ሚካኤል የተባሉ የአሉላ ዱላ እንደ ቀመሱ አሽከሮቻቸው ድምጥማጣቸው ጠፍተው ደጃቱ ወደ ደብረ ባዚን ገዳም ሸሽተው ይደበቃሉ፣ የደብረ ባዚን መነኩሳትም ከራስ አሉላ በማስታረቅ ሂወታቸውን እንዲያድኑ ይማፀናሉ፡ መነኮሳቱ ደጃት ወልደ ሚካኤልን ይዘው ወደ ራስ አሉላ በመውሰድ ምሕረት እንዲጠይቁ አደረጉ ፡፡ ጀግና ርህሩህ ነው እንደሚባለው አጥፍቻለሁ ምሕረት ይደረግልኝ ያለ አልምርም አይባልም በእኔ በኩል ይቅር ብየሃለሁ ሆኖም አባታችን አፄ ዮሃንስ ይቅር ሊሉህ ስለሚገባ ወደ ቤተመንግስት መቐለ ትሄዳለህ አሉአቸው፡፡እንዲሁም አደረጉ ፡፡አፄ ዮሃንስም ተቀበሉአቸው፡፡

አፄ ዮሃንስም ምህረት አድራጊ ጀግና ነበሩና ምህረታቸው አልነፈጉአቸውም ፡፡ ሆኖም ምህረታቸው በመኳዋንቱና በጦር ጀኔራሎቻቸው ሊታመንበት እንደሚገባ አምነውበት ጉዳዩ ለምክክር ወደ ባለሙዋሎቻቸው መኳዋንንቶች አቀረቡት ፡፡ጉዳዩ ስሜት የሚነካ ነበርና አፄ ዮሃንስ አሳማኝ ሆነው መገኘት ይጠበቅባችው ነበር፡፡ ቀጥሎ ያለው የውይይት ይዘት ተመልከቱ አባቶቻችን ጀግና ተዋጊና አዋጊ ብቻ ሳይሆኑ የተካኑ የፖለቲካ ጠበብት መኖራቸው ትገነዘባላቸው ብየ እገምታለሁ ፡፡ አፄ ዮሃንስ 4 ኛ

“ልጆቼ ወዳጆቼ !

“ ሐሳባችሁን ደርሼበታለሁ ፣ወልደ ሚካኤልን እኔን ብቻ አልበደለም፣ ሁላችንም አሳዝኖአል፡፡ ከሁላችን ጋር ደም ተቃብቶአል ትውልድ የማይረሳው በደል በድሎአል፡፡የራስ ባርያውያን ያህል አዛውንት ደም አፍስሶአል፡፡ቀደም ሲልም ደጃዝማች ሃይሉን ያህል ሰው ገድሎአል፡፡እንግዲህ የሾምኩአቸውን ሁሉ ከመግደል የበለጠ ድፍረትና በደል ምን አለ? ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎ መሓላውን አፍርሶ ጭፍራውን ሁሉ ሰብስቦ ከግብፅ ጎን ተሰልፎ ኢትዮጵያን ወጋት ፡፡ እናቱን በደላት፡፡ በደሉን መቼም ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡

“ ለአገራችን አንድነት ስንል ግን ምሕረትንና ትእግስትን ገንዘባችን ማድረግ ተገቢ ነው ፡፡የአፄ ቴወድሮስ ሃይል እንኩትኩት ብሎ ብቻቸውን የወደቁት መኳዋንንቱ በየፊናቸው በመነጣጠሉ ነው፡፡ እኛም ብዙ ጠላት አለብን፡፡የውጭ ጠላት ገና በበጎስና በምጥዋ እንደሰፈረ ነው፡፡ከዚህ ሌላ ደግሞ በውስጣችን ያለውን ነገር ታውቁታላችሁ፡፡

“ አሁን ወልደ ሚካኤልን ምሕረት ብንነሳው አገር መለያየት ይጀምራል፡፡ያኮረፈ ሁሉ በዚያው ይቀራል፡፡ የኛው መነጣጠልም በዳር ሆኖ ለሚጠባበቅ ጠላት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ አሁንም ሁላችሁም ብትሆኑ ወልደሚካኤልን ‘ይቅር’ በሉት ታረቁት አቅርቡት፡፡እኔም ይቅር ያልኩት እናንተም ይቅር ብላችሁ እንድትታረቁት ብየ ነውና ታረቁት ምከሩት” ብለው ጠየቁ፡፡

መኳዋንንቱም ከልባቸው የገባና የሚያምኑበት መሆናቸው ስላረጋገጡላቸው ወልደ ሚካልን አስቀርበው ከመኳዋንቱና ከ ጦር አለቆቹ አስታረቁዋቸው፡፡

ከእርቁ በሁዋላ መኳዋንቱና የጦር አለቆቹ ሲወጡ ራስ አርአያ ወደ አፄ ዮሃንስ ቀረብ ብለው

“ ምሕረት ማድረጉና መታረቁ ተገቢ ነው ስለ መተዳደርያውስ ምን አስብክለት ብለው ጠየቁአቸው፡፡
እርስዎ ምን ያስባሉ ወደ ሃገሩ ይመለስ ይግባ ወይስ እዚሁ ይሰንብት ብለው መልሰው ጠየቁአቸው አፄ ዮሃንስ ለአጎታቸው ራስ አርአያን፡፡
“ አገሩን ብትሰጠው መልካም ነው፡፡ለጊዜው ከአሉላ ስር ሆኖ አሉላን እየጠበቀውና እየረዳው ቢቆይ የሚሻል ይሆናል” አሉ ራስ አርአያ፡፡
“አሉላን ከምንድነው የሚጠብቀው ”አሉ አፄ ዮሃንስ በመጠራጠር ስሜት ሆነው፡፡ሁሉ ጊዜ የዋህነት አያዋጣም አሉላም ቢሆን ከቤታቸው ከገባ በሁዋላ የአምለሱን እጅ ከሰጠነው ወዲህ የምሰማበት አንዳንድ ጉዳይ አለና ከኛ ርቆ ብቻውን ሆኖ የሚሰራውን የሚመለከት ያስፈልገዋልና ወልደሚካኤልን ራስ ብለህ ከአሉላ ስር ሆኖ እንዲጠብቀው ቢደረግ ይሻላል” አሉዋቸው፡፡
አፄ ዮሃንስ የአጎታቸው ምክር ከልባቸው አሳደርዋት ፡፡.... በዚሁ መሰረት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን ራስ ብለው በራስ አሉላ ስር ሆነው ሓማሴንን እንዲገዙ ሾሙአቸው፡፡ ራስ ሚካኤልም ለአፄ ዮሃንስ ብቻ ሳይሆን ለራስ አሉላም ፍፁም ባለ ውለታና ፍፁም ታማኝ መሆናቸውን በመሃላ አረጋገጡ፡፡
በማሞ ውድነህ “አሉላ አባ ነጋ” በሚል በ 1979 ዓ/ምበኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ካሳተሙት መፅሐፋቸው የተወሰደ /ገፅ 89-90 ይመልከቱ/
እንግዲህ አማካሪ ከተባለም እንደ ራስ አርአያ ያለ ብልህና አርቆ አሳቢ ልበል! አዎ ፣ ትግራይ እንዲህ ያሉ አርቆ አሳቢ የፖለቲካ መሪዎችም ለሃገራችን ኢትዮጵያ አበርክታለች። ከዚህ የምንማረው የጠላት ስራ የሰራ ሁሉ የጥላቻ በትር ታሳርፍበታለህ ማለት እንዳልሆነና ጥላቻን በፍቅር በማሸነፍ ለሃገር የሚበጅ ግዙፍ ቁምነገር መስራት እንደሚቻል ሲሆን አፄ ዮሃንስና ባለስልጣኖቻቸው ተደማምጠው ተመካክረው ያሳዩት ሆደ ሰፊነት ታላቋን ኢትዮጵያ በክብር አስረክበው ለማለፍ ያበቃቸው የአመራር ብቃታቸው እነሆ ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ ለዘላለሙ ክብርና ሞገስ ለብሶ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህሊና የክብር ቦታ ተሰጥቶት ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ ይገኛል ።
ከአፄ ዮሃንስ ቀደምት የነበሩት ራስ ወልደ ስላሴም ዋና ከተማቸው ከመቐለ በእግር የሁለት ሰአት መንገድ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በምትገኘዋ ጨለቆት ዋና ከተማቸው አድርገው መላውን አቢሲኒያ ሲያስተዳድሩ ጥላቻን በፍቅር ማሸነፍ የሚለው መርህ በሚገባ የተገበሩ ነበሩ ።
አባታቸውን ከገደሉ ቤተሰቦች ለከፍተኛ ስልጣን ሾሙ ። አዎ ሾሙ !
የአሁኑ ፖለቲካችንስ ከአፄ ዮሃንስ የፖለቲካ ዶክትሪን ሲመዘን ምን ይመስላል ? ስማቸውን የሚዘክር ሃውልት ለማሰራት ዳተኛ መሆኑንስ አይደንቅም ? የአፄ ዮሃንስን ስም ለማጉደፍ የሚፍጨረጨሩ ጨለምተኞችስ ? በዘመንኛው ዴሞክራሲኛ መቻቻል የሚባለው በአባቻችን ታሪክ ትልቅ ቦታ የነበረው መሆኑን ተገንዝበን ከፖለቲካ ታሪካችን የፖለቲካ እውቀትና ክህሎት ለመማር ዝግጁነታችን ምን ይመስላል? እንደ ዜጋ ከታሪክ ያለን መራራቅ ልናስብበት ይገባል፡፡

http://www.ethiopanorama.com